# መግቢያ

አስተዳደራዊ ጥፋቶች በህግ የተደነገጉ ግዴታዎችን ባለመፈጸም /ባለመወጣት/ የሚፈጸሙ ጥፋቶች ሲሆኑ የወንጀል ጥፋት ደግሞ በህግ የተከለከሉ ድርጊቶች መፈጸም ወይም አድርግ የተባለውን አለማድረግ ነው። አንድን ድርጊት መፈጸም ወይም አለመፈጸም አስተዳደራዊ ቅጣት እና የወንጀል ኃላፊነት የሚያስከትል በሚሆንበት ጊዜ ጥፋቱን የፈጸመው ሰው አስተዳደራዊ ቅጣት መቀጣቱ የወንጀል ተጠያቂነቱን አያስቀርም። ማንኛውም ታክስ ከፋይ አስተዳደራዊ ቅጣት የተጣለበት እና/የወንጀል ክስ የቀረበበት መሆኑ መክፈል የሚገባውን ታክስ የመክፈል ግዴታውን አያስቀርም።

**በሥራ ሂደት መብትና ግዴታን አውቆ መሥራት ለታክስ የአስተዳደር እና የወንጀል ቅጣት ከመቀነስ በሻገር ያሸልማል። በመሆኑም፤ በዚህ ሞጁል፤ የታክስ ከፋዮች መብት እና ግዴታ፣** በታክስ ውሳኔ አለመግባባት ሲፈጠር በየደረጃው አቤቱታ የሚቀርብበትን ሂደት፣ በታክስ የሚፈጸሙ የአስተዳደራዊ እና የወንጀል ቅጣቶች እንዲሁም ሽልማቶች በተጨማሪ **አስተዳደራዊ ቅጣት አነሳስ** ዙሪያ የተዘጋጀ ጽሑፍ እንደሚከተለው ቀርቧል።

## ክፍል አንድ
## አጠቃላይ ሁኔታ

### **1.1.** ዓላማ

ዋና ዓላማ

**ከትምህርቱ በኋላ ሠልጣኞች፤**

**በታክስ አስተዳደር ሕጉ በመወያየት በሕጉ የተቀመጡ መብትና ግዴታዎችን በመለየት በታክስ ውሳኔ ላይ** አለመግባባት ሲፈጠር በቅደም ተከተል ምን ምን መደረግ እናዳለበት ለይተው በታክስ ለሚፈጸሙ የአስተዳደራዊ እና የወንጀል ቅጣቶች እንዲሁም ሽልማቶችን ይረዳሉ።

ዝርዝር ዓላማ

- ✓ የታክስ ከፋዩን መብት እና ግዴታ ይለያሉ፤
- ✓ በታክስ ውሳኔ አለመግባባት ሲፈጠር በየደረጃው አቤቱታ የሚቀርብበትን ሂደት ይዘረዝራሉ፤
- ✓ በታክስ የሚፈጸሙ የአስተዳደራዊ እና የወንጀል ቅጣቶች እንዲሁም ሽልማቶች ዙሪያ ገለጻ ማድረግ ይችላሉ፤
- ✓ **አስተዳደራዊ ቅጣት በከፊል ወይም ሙሉ በሙሉ የሚነሳባቸውን እና የማይነሳባቸውን ምክንያቶች ይዘረዝራሉ።**

## 1.2. ውጤት

ሠልጣኞች የሚጠበቅባቸውን ግዴታና መብት ተረድተው፤ ግዴታቸውንና ኃላፊነታቸውን በቀላሉ እንዲወጡ እና በታክስ ሕጉ ላይ ግልጽነት እንዲፈጠር በማድረግ በአገልግሎት አሰጣጡ የሚፈጠር አለመግባባት ሲፈጠር የሚፈቱበትን መንገድ በመለየት እና የታክስ ሕጉን አለማክበር የሚያስከትለውን የሕግ ኃላፊነት ይረዳሉ።

## 1.3. ወሰን

### 1.3.1. የሰነዱ ሽፋን

የሰነዱ ሽፋን የታክስ አስተዳደር አዋጅ 983/2008 እና *መመሪያ* **ቁጥር** 137/2010 **ነው።**

### 1.3.2.የሥልጠና ተሳታፊዎች

ሥልጠናው በሥርዓቱ ውስጥ ላሉ ግብር ከፋዮች በዘርፋቸው በመለየት የሚሰጥ ሲሆን የድርጅቱ/ፒኤልሲው ኃላፊ እና የፋይናንስ ክፍል ሠራተኞች እንዲሁም የታክስ እንደራሴዎች የሚሠለጥኑ ይሆናል።

### 1.3.3.ጊዜ

ሥልጠናው የሚሰጠው ለሶስት ሰዓታት ነው።

## 1.4. ትርጓሜ

*ትርጉም የሚያስፈልጋቸው ቃላትና ሀረጎች በፌደራል የታክስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር* 983/2008 *ክፍል አንድ አንቀጽ የተሰጣቸውን ትርጉም እና የታክስ አስተዳደር ቅጣት አነሳስ መመሪያ ቁጥር* 137/2010 የተሰጠ ትርጉም *ይይዛሉ።*

## ክፍል ሁለት
## ከታክስ ጋር በተገናኘ የሚፈጠር አለመግባባት

ተገልጋዮች በሥራ ላይ ስላሉ የታክስ ድንጋጌዎች፣ ተቋሙ ስለሚሰጣቸው አገልግሎቶችና ቅድመ ሁኔታዎች ተገቢውን መረጃ እንደ አግባብነቱ በስልክ፣ በድረ ገጽ እና በአካል በመቅረብ መረጃዎቹን የመጠየቅ፣ ምላሽ የማግኘት እና አገልግሎቶቹን የመጠቀም መብት አላቸው። ከዚህ በተጨማሪ ማንኛውም የተቋሙ ተገልጋይ በጾታ፣ በዘርና ቋንቋ፣ በሃይማኖት፣ በማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ደረጃው እና መገለል አድልዎ ሳይደርስበት በተገቢው ሁኔታ አገልግሎት የማግኘት መብት አለው። ከዚህ ባሻገር
ማንኛውም ተገልጋይ ክብሩና ስብዕናው ተጠብቆ የመስተናገድ መብት ያላቸው ሲሆን ማንኛውም የታክስ ግዴታ የሚመለከተው ሰው/ ድርጅት፤ በሚኒስቴሩ የተፈቀደ ደረሰኝ የማሳተምና የመጠቀም፣ ለታክስ ተገቢነት ያላቸው ሰነዶችን በሕጉ ለተመለከተው ጊዜ ያህል ይዞ የመቆየት ግዴታ አለባቸው። መብት እና ግዴታን አውቆ መሥራት አለምግባባትን እና በአለመግባባት የሚፈጠር አስተዳደራዊ እና የወንጀል ቅጣቶችን ይቀንሳል።

ሙከራ አንድ

1. የታክስ ከፋዩን መብት እና ግዴታ አብራሩ?

## 2.1. ከታክስ ጋር በተገናኘ የሚፈጠር አለመግባባት **(983/2008** ክፍል ዘጠኝ**)**

በታክስ ሕግ መሠረት የቀረበን ማንኛውም ማመልከቻ ባለሥልጣኑ ሳይቀበለው በሚቀርበት ጊዜ አለመቀበሉን የሚገልጸው ማስታወቂያ ማመልከቻውን ያልተቀበለበትን ምክንያቶች መግለጫ ያካተተ መሆን አለበት።

### **2.1.1.** የታክስ እና ይግባኝ የሚቀርብባቸው ውሳኔዎች የመጨረሻ ስለመ□ናቸው **(983/2008** አ**. 53)**

I. በዚህ ክፍል በተደነገገው ሥነ-ሥርዓት መሠረት ካልሆነ በስተቀር፦

ሀ) የታክስ ወይም ይግባኝ ሊቀርብበት የሚችል ውሳ□ ወሳኝ እና የመጨረሻ በመሆኑ በማናቸውም ሁኔታ በኮሚሽኑ ወይም በፍርድ ቤት ወይም በሌላ የዳኝነት ሥነ-ሥርዓት ተቃውሞ ሊቀርብበት አይችልም።

ለ) የታክስ ስሌት ማስታወቂያ ወይም ውሳኔ ወይም በባለሥልጣኑ እንደ ታክስ ስሌት ማስታወቂያ ወይም ውሳኔ ቅጂ የተረጋገጠ ሰነድ ማቅረብ የታክስ ስሌት ማስታወቂያው ወይም ውሳኔው በአግባቡ የተሰጠ ስለመሆኑ እንዲሁም በታክስ ስሌት ማስታወቂያው ወይም ውሳኔው የተመለከተው የታክስ መጠን እና ሌሎች ዝርዝር ጉዳዮች ትክክለኛ ስለመሆናቸው ወሳኝ ማስረጃ ነው እንዲሁም

ሐ) ታክስ ከፋዩ ራሱ የሚያሰላውን ታክስ በተመለተ ታክስ ከፋዩ ራሱ ያሳወቀበትን ዋናውን የራስ ታክስ ስሌት ማስታወቂያው ወይም በባለሥልጣኑ እንደራስ ታክስ ስሌት ማስታወቂያው ዋናው ቅጂ የተረጋገጠ ሰነድ ማቅረብ ስለማስታወቂያው ይዘት ወሳኝ ማስረጃ ነው።

II. ባለሥልጣኑ ለታክስ ከፋይ የታክስ ስሌት ወይም ውሳኔ ማስታወቂያ በኤሌክትሮኒክስ ዘዴ የሚቀርብበት ጊዜ፣ በተራ ቁጥር I /ለ/ የተመለከተው የታክስ ስሌት ማስታወቂያ ወይም ውሳኔ ቅጂ ማስታወቂያ ወይም ውሳኔውን በመለየት እና በኤሌክትሮኒክስ ዘዴ የተላለፈው የታክስ ስሌት ማስታወቂያ ወይም ውሳኔ ዝርዝር ጉዳዮች በመግለጽ በባለሥልጣኑ የተረጋገጠ ሰነድ ይጨምራል።

III. ታክስ ከፋይ የራስ ታክስ ስሌት ማስታወቂያ በኤሌክትሮኒክስ ዘዴ በሚያቀርብበት ጊዜ በተራ ቁጥር I /1/ ሐ/ የተመለከተው የራስ ታክስ ስሌት ማስታወቂያ ቅጂ ማስታወቂያውን በመለየት እና በኤሌክትሮኒክስ ዘዴ የተላለፈውን የራስ ታክስ ስሌት ማስታወቂያ ዝርዝር ጉዳዮች በመግለጽ በባለሥልጣኑ የተረጋገጠን ሰነድ ይጨምራል።

### **2.1.2.** በታክስ ውሳኔ ላይ ስለሚቀርብ የቅሬታ ማስታወቂያ **(983/2008** አ**. 54)**

I. በታክስ ውሳኔ ቅር የተሰኘ ታክስ ከፋይ የውሳኔውን ማስታወቂያ በደረሰው በ 21 ቀናት ውስጥ በውሳኔው ላይ የቅሬታ ማስታወቂያ ለባለሥልጣኑ በጹሑፍ ማቅረብ ይችላል።

II. ቅርታ የቀረበበት የታክስ ውሳኔ በተሻሻለ የታክስ ስሌት ላይ ከሆነ የታክስ ከፋዩ ውሳኔ በተሻሻለ የታክስ ስሌት የመቃወም መብት የመጀመሪያ ውሳኔ የታክስ የመቃወም መብት የመጀመሪያውን የታክስ ስሌት የመቃወም መብት የመጀመሪያውን የታክስ ስሌት በመለወጥ፣ በመቀነስ ወይም በመጨመር በተደረገው ማሻሻያ ላይ ብቻ የተገደበ ይሆናል።

III. በተራ ቁጥር I መሠረት በታክስ ከፋይ የቀረበ የቅሬታ ማስታወቂያ በአግባቡ እንደቀረበ የሚቆጣጠረው ከዚህ በታች የተዘረዘሩት ቅድመ ሁኔታዎች ሲሟሉ ብቻ ነው፡፡

ሀ. የቅርታ ማስታወቂያው ታክስ ከፋዩ የታክስ ውሳኔውን ለማስተከከል ሊደረጉ ይገባል ብሎ የሚያምንባቸው ማሻሻያዎች እና እነዚህን ማሻሻያዎች ማድረግ አስፈላጊ የሆነበትን ምክንያቶች በትክክል የሚገልጽ ከሆነ፣

ለ. ቅረታው ከታክስ ስሌት ጋር የተገናኘ ከሆነ ታክስ ከፋዩ በታክስ ስሌት መሠረት መክፈል ያለበትን እና በቅሬታ ማስታወቂያው ተቃውሞ ያላቀረበበትን ታክስ የከፈለ እንደሆነ እንዲሁም

ሐ. በታክስ ውሳኔው ላይ ቅሬታ ቢኖረውም ታክሱን ከፍሎ የቅሬታ ማስታወቂያ ማቅረብን የመረጠ ከሆነ የተወሰነበት ታክስ ከከፈለ ነው፡፡

IV. ባለሥልጣኑ የቅሬታ ማስታወቂያው በአግባቡ አልቀረበም ብሎ ሲያምን ለታክስ ከፋዩ የሚከተሉትን የሚገልጽ የጽሑፍ ማስታወቂያ ወዲያውኑ ይሰጠዋል፡-

ሀ. ቅረታው በአግባቡ አልቀረበም የሚልባቸው ምክንያቶች እና

ለ. ከሚከተሉት በዘገየው ጊዜ ውስጥ ታክስ ከፋዩ ቅሬታውን ካላቀረበ የቅሬታ ማቅረቢያ ጊዜ ውስጥ ታክስ ከፋዩ ቅሬታውን ካላቀረበ የቅሬታ ማቅረቢያ ጊዜ እንደሚያልፍ፣

- ቅሬታው የሚመለከተው የታክስ ውሳኔ ማስታወቂያ በደረሰው በ 21 ቀናት ውስጥ ወይም
- በዚህ መሠረት የሚሰጠው ማስታወቂያ በደረሰው በ 1 0 ቀናት ውስጥ፡፡

V. በተራ ቁጥር IV መሠረት የቅሬታ ማቅረቢያ ጊዜ ያለፈ ከሆነ ባለሥልጣኑ ይህንን የሚገልጽ የጽሑፍ ማስታወቂያ ለሚመለከተው ታክስ ከፋዩ ይሰጣል፡፡

VI. በተራ ቁጥር I መሠረት ማመልከቻ ሲቀርብ፣ ባለሥልጣኑ፡-

ሀ. ታክስ ከፋዩ በኢትዮጵያ ውስጥ ያልነበረ በመሆኑ በህመም ምክንያት ወይም በሌላ አጥጋቢ ምክንያት በተራ ቁጥር I ወይም /IV/ በተወሰነው ጊዜ ውስጥ የቅሬታ ማስታወቂያውን ማቅረብ አለመቻሉ እና

ለ. የቅረታ ማስታወቂያውን ለማቅረብ በታክስ ከፋዩ በኩል ምክንያታዊ ያልሆነ መዘግየት አለመኖሩ ሲያምንበት በተራ ቁጥር I የተመለከተው የቅሬታ ማቅረቢያ ጊዜው ካበቃበት ቀን ጀምሮ ከ 1 0 ቀናት ላልበለጠ ጊዜ ሊያራዝም ይችላል፡፡

### **2.1.3.** በቅሬታ ላይ ውሳኔ ስለመስጠት **(983/2008 አ. 55)**

I. ባለሥልጣኑ በታክስ አስተዳደር አዋጅ አንቀጽ 58 መሠረት በአግባቡ የቀረቡ ቅሬታዎችን በነጻነት በመመርመር በቅሬታዎቹ ላይ ለሚሰጠው ውሳኔ የውሳኔ ሀሳብ የሚቀርብ ቋሚ የሥራ ከፍል ያቋቁማል፡፡

II. ባለሥልጣኑ፣ ቅሬታዎች የሚታዩበትን ሥነ-ሥርዓት እና ለባለሥልጣኑ የሚቀርቡ የውሳኔ ሃሳቦች የሚመሠረትረባቸው ጉዳዮች እና የውሳኔ አሰጣጡን ሥርዓት የያዘ ዝርዝር መመሪያ ያወጣል፡፡

III. የሥራ ክፍሉ በታክስ ስሌት ላይ የቀረበውን ቅሬታ ሲመረምር በታክስ ስሌቱ የተመለከተው በታክስ መጠን ሊጨምር ይገባል የሚል እምነት ሲኖረው፣ የሥራ ክፍሉ የታክስ ስሌቱ ለሚመለከተው የታክስ ሠራተኛ ተመልሶ እንደገና እንዲታይ የውሳኔ ሃሳብ ለባለሥልጣኑ ማቅረብ ይኖርበታል፡፡

IV. ባለሥልጣኑ በሥራ ክፍሉ የቀረበውን የውሳኔ ሃሳብ ከመረመረ በኋላ የቀረበውን ቅሬታ በሙሉ ወይም በከፊል በመቀበል ወይም ውድቅ በማድግ ውሳኔ የሚሰጥ ሲሆን ውሳኔውም "በቅሬታ ላይ የተሰጠ ውሳኔ" ተብሎ ይጠቀሳል።

V. ባለሥልጣኑ በቅሬታ ላይ የሰጠውን ውሳኔ ለታክስ ከፋዩ በጹሑፍ የሚያሳውቀው ሲሆን በታክስ ስሌት ላይ የቀረበ ቅሬታ ከሆነ የታክስ ስሌት ላይ የቀረበ ቅሬታ ከሆነ የታክስ ስሌቱን ማሻሻል ጨምሮ ውሳኔውን ለማስፈፀም አስፈለጊ የሆኑትን እርምጃዎች ይወሰዳል።

VI. ቅረታ ላይ የተሰጠ ውሳኔ ማስታወቂያ የጉዳዩን ዋና ፍሬ ነገሮች፣ ግኝቶች እና በውሳኔ መሠረት የሆኑትን ምክንያቶች እና ለኮሚሽኑ ይግባኝ ማቅረብ እንደሚቻል የሚገልጽ መግለጫ ማካተት አለበት።

VII. ታክስ ከፋዩ ቅረታ ካቀረበበት ቀን ጀምሮ ባሉት 180 ቀናት ውስጥ ባለሥልጣኑ በቅርታው ላይ ውሳኔ ካልሰጠ ታክስ ከፋዩ ይግባኙን 180 ቀን በተጠናቀቀ በ30 ቀናት ውስጥ ለታክስ ይግባኝ ኮሚሽን ማቅረብ ይችላል።

### 2.1.4. ለታክስ ይግባኝ ኮሚሽን ይግባኝ ስለማቅረብ **(983/2008 አ. 56)**

I. ይግባኝ ሊቀርብበት በሚችል ውሳኔ ላይ ቅር የተሰኘ ታክስ ከፋይ በታክስ አስተዳደር አዋጅ አንቀጽ 76 መሠረት የይግባኝ ማስታወቂያውን ለታክስ ይግባኝ ኮሚሽን ሊያቀርብ ይችላል።

II. በታክስ ስሌት ላይ ከቀረበ ቅሬታ ጋር በተገናኘ በታክስ ከፋይ ለታክስ ይግባኝ ኮሚሽን የሚቀርብ የይግባኝ ማስታወቂያ በአግባቡ ቀርቧል ሊባል የሚችለው በክርክር ላይ ያለ ታክስ 50% የተከፈለ እንደሆነ ብቻ ነው።

III. በተራ ቁጥር II " በክርክር ላይ ያለ ታክስ" ከታክሱ ጋር በተገናኘ ሊከፈል የሚገባውን ቅጣትና የዘገየ ክፍያ ወለድን አይጨምርም።

IV. የታክስ ይግባኝ ኮሚሽን ተራ ቁጥር I መሠረት የይግባኝ ማስታወቂያ የሚቀርብበት ጊዜ እንዲራዘም ስለሚቀርብ ማመልከቻ መመሪያ ሊያወጣ ይችላል።

### **2.1.5.** ለፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ስለማቅረብ **(983/2008 አ. 57)**

I. ለኮሚሽኑ በቀረበ የታክስ ይግባኝ ተካፋይ የነበረ ሰው ኮሚሽኑ በሰጠው ውሳኔ ቅር የተሰኘ እንደሆነ የኮሚሽኑ የውሳኔ ማስታወቂያ በደረሰው በ30 ቀናት ውስጥ የይግባኝ ማስታወቂያውን ለፌዳራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሊያቀርብ ይችላል።

II. በኮሚሽኑ በታየ የታክስ ይግባኝ ላይ ተከራካሪ የነበረ ሰው በተራ ቁጥር I የተመለከተው የይግባኝ ማቅረቢያ ጊዜ እንዲራዘምለት በጹሑፍ ማመልከቻ ሲጠይቅ ለፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ጊዜውን ሊያራዝመው ይችላል።

III. በታክስ ስሌት ላይ ከቀረበ ቅሬታ ጋር በተገናኘ በታክስ ከፋይ ለፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ፍርድ ቤት የሚቀርብ የይግባኝ ማስታወቂያ በአግባቡ ቀርቧል ሊባል የሚችለው በክርክር ላይ ያለ ታክስ 75% የተከፈለ እንደሆነ ብቻ ነው።

IV. ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ የሚቀርበው በሕግ ጉዳዮች ላይ በቻ ሲሆን የይግባኝ ማስታወቂያውም በቀረበው ይግባኝ የሚነሱት የሕግ ጉዳዮች መግለጽ አለበት።

V. የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኙን በመስማት፡-

ሀ. የኮሚሽኑ ውሳኔ ሊያጸናው፤

ለ. የኮሚሽኑ ውሳነ በመሻር፡-

i. የኮሚሽኑ ውሳኔ የሚተካ ውሳኔ ሊሰጥ ወይም

ii. ፍርድ ቤቱ በሚሰጠው መመሪያ መሠረት ጉዳዩ እንደገና እንዲታይ ለኮሚሽኑ ወይም ለባለሥልጣኑ መልሶ ሊልከው፤

ሐ. ይግባኙን ውድቅ ሊያደርገው ወይም

መ. ተገቢ መስሎ የታየውን ሌላ ውሳኔ ሊሰጥ ይችላል።

VI. በዚህ ተራ ቁጥር III "በክርክር ላይ ያለ ታክስ" ማለት የታክስ ይግባኝ ኮሚሽኑ እንዲከፈል ውሳኔ የሰጠበት እና ታክስ ከፋዩ በይግባኝ ማስታወቂያ ቅሬታ ያቀረበበት ታክስ ሲሆን ከታክሱ ጋር በተገናኘ ሊከፈል የሚገባውን ቅጣትና የዘገየ ክፍያ ወለድን አይጨምርም።

## 2.1.6. ለፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ስለሚቀርብ ይግባኝ (983/2008 አ. 58)

i. ለፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በቀረበ የታክስ ይግባኝ ተከፋይ የነበረ ሰው ፍርድ ቤቱ በሰጠው ውሳኔ ቅር በተሰኘ እንደሆነ የፍርድ ቤቱ የውሳኔ ማስታወቂያ በደሰው በ 3 0 ቀናት ውስጥ የይግባኝ ማስታወቂያውን ለፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሊያቀርብ ይችላል።

ii. በፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በታየ የታክስ ይግባኝ ላይ ተከራካሪ የነበረ ሰው ተራ ቁጥር i የተመለከተው የይግባኝ ማቅረቢያ ጊዜ እንዲራዘምለት በጹሑፍ ማመልከቻ ሲጠይቅ የፌዳራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ጊዜውን ሊያራዝመው ይችላል።

## 2.1.7. የማስረዳት ኃላፊነት (983/2008 አ. 59)

ከታክስ ውሳኔ ጋር በተገናኘ በሚደረገው ማንኛውም የታክስ ክርክር ሂደት የታክስ ውሳኔ ትክክል አለመሆኑን የማስረዳት ኃላፊነት የታክስ ከፋዩ ነው።

## 2.1.8. የታክስ ይግባኝ ኮሚሽን ወይም የፍርድ ቤት ውሳኔ ስለመፈፀም (983/2008 አ. 60)

ባለሥልጣኑ የታክስ ይግባኝ ኮሚሽን የፌዳራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ወይም የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ወይም የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ውሳኔ በደረሰው 3 0 ቀናት ውስጥ የተሻሻለ የታክስ ስሌት ማስታወቂያ ለታክስ ከፋዩ መስጠትን ጨምሮ እርምጃዎችን መውሰድ አለበት።

በታክስ አስተዳደር አዋጅ አንቀጽ 26 የተመለከተው የተሻሻለ የታክስ ስሌት የጊዜ ገደብ የታክስ ይግባኝ ኮሚሽን ወይም የፍርድ ቤት ውሳኔን ተግባራዊ ለማድግ በሚከናወን የታክስ ስሌት ማሻሻያ ላይ ተፈፃሚ አይሆንም።

መከራ ሁለት

1. በታክስ ውሳኔ አለመግባባት ሲፈጠር በየደረጃው አቤቱታ የሚቀርብበትን ሂደት አብራሩ?

ክፍል ሶስት

የታክስ አስተዳደር እና የወንጀል ቅጣቶች

## III.1. አስተዳደራዊ ቅጣቶች

### III.1.1. በታክስ ከፋይነት ባለመመዝገብ

- በታክስ ከፋይነት መመዝገብ ሲገባው ያልተመዘገበ እንደሆነ መመዝገብ ከነበረበት ጊዜ እስካመለከተበት መክፈል ያለበትን ታክስ 25% መቀጮ (በዚህ ጊዜ ውስጥ የሚከፈል ግብር ከሌለ ለየወሩ ብር 1,000 ቅጣት) ይከፍላል፤
- ከግብር ከፋይነት እንዲሰረዝ ያልጠየቀ ለየወሩ ብር 1,000 መቀጫ ይከፍላል፣

ምንጭ:- ታክስ አስተደደር አዋጅ ቁጥር **983/2008** አንቀ**.101 (1-4)**

### III.1.2. ሰነዶችን ባለመያዝ የሚጣል ቅጣት /Financial statement/

- በታክስ ሕግ መሠረት መያዝ የሚጠበቅበትን ማንኛውንም ሰነድ ያልያዘ ታክስ ከፋይ ሰነዱ መያዝ በነበረበት የታክስ ዘመን መክፈል ያለበትን ታክስ 20% ቅጣት ይከፍላል፤
- መክፈል የሚኖርበት ታክስ የሌለ እንደሆነ ለገቢ ግብር ሲሆን ብር 50 ሺ፤ ለሌላ ታክስ ሲሆን ብር 2 ሺ የሂሳብ ሰነድ ላልያዘበት ለእያንዳንዱ የታክስ ዘመን ቅጣት ይከፍላል፤
- ከሁለት ዓመት በላይ የሂሳብ ሰነድ ያለመያዝ የንግድ ፈቃድ ስረዛን ያስከትላል፣

ምንጭ:- ታክስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር **983/2008** አንቀጽ **102 (1-6)**

### III.1.3. በታክስ ከፋይ መለያ ቁጥር መቅጣት

i. የታክስ ከፋይ መለያ ቁጥሩን (በታክስ ደረሰኝ፣ በታክስ ዴቢት ክሬዲት ማስታወሻ፣ በታክስ ማስታወቂያ ወይም በሌላ በማንኛውም ሰነድ ላይ) ሳይገልጽ የቀረ ታክስ ከፋይ የታክስ ከፋይ መለያ ቁጥር ባልተገለጸበት በእያንዳንዱ ሰነድ ብር 3 ሺ ቅጣት ይከፍላል፤

**ii.** **TIN** አሳልፎ የሰጠም ሆነ የሌላን የተጠቀመ ብር **10,000**፤

- ከላይ በተራ ቁጥር i እና ii በተጠቀሱት ድርጊቶች ምክንያት ታክስ ከፋዩ ወይም ሌላ ሰው ያገኘው የገንዘብ ጥቅም ከብር 10 ሺ የሚበልጥ ከሆነ የሚከፍለው የገንዘብ ቅጣት መጠን ካገኘው ጥቅም ጋር እኩል ይሆናል፤

ምንጭ:- ታክስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር **983/2008** አንቀ**.103 (1-3)**

### III.1.4. የታክስ ማስታወቂያ ዘግይቶ ማቅረብ (late Declaration) መቀጮ

- በሕግ በተወሰነው ጊዜ ውስጥ የታክስ ማስታወቂያ ግዴታውን ያልተወጣ ታክስ ከፋይ ለዘገየበት ለእያንዳንዱ የታክስ ጊዜ ያልተከፈለውን ታክስ 5%፤ 25% እስኪሞላ ድረስ ቅጣት ይከፍላል፤
- ገና ጀማሪ የሂሳብ ሰነድ ያዥ ከሆነና ለመጀመሪያው የሒሳብ ጊዜ የታክስ ማስታወቂያ ያላቀረበ ሰው ቅጣት ከብር 50 ሺ አይበልጥም።

ምንጭ:- ታክስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር **983/2008** አንቀጽ **104(1-3)**

### III.1.5. ዘግይቶ መክፈል የሚያስከትለው (Late Payment) ቅጣት

- ማንኛውም ታክስ ከፋይ በታክስ መክፈያ ጊዜው ውስጥ ታክስ ሳይከፍል ከቀረ ለዘገየበት ጊዜ፦

i. ለአንድ ወር (ከፊል) ጊዜ ባልተከፈለው ታክስ ላይ 5% እና

ii. ከዚያ በኋላ ለዘገየበት ለእያንዳንዱ ወር ለሆነው ጊዜ ባልተከፈለው ታክስ ላይ ተጨማሪ 2% ቅጣት ይከፈላል፤

- በተራ ቁጥር i እና ii ቅጣት ከዋናው የታክስ ዕዳ መብለጥ የለበትም፤

ምንጭ:- ታክስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር **983/2008** አንቀጽ **105 (1-2)**

### III.1.6. ከተከፋይ ሒሳብ ላይ ተቀንሶ ከሚከፈል (Withholding payable)

- ከተከፋይ ሒሳብ ላይ ታክስ ቀንሶ ለባለሥልጣኑ ማስተላለፍ ያለበት ማንኛውም ሰው ሳይቀንስ የቀረውን ወይም ቀንሶ ለባለሥልጣኑ ያላስተላለፈውን ታክስ 10% ቅጣት ይከፍላል፤
- ከዚህ በተጨማሪ ታክስ ተቀንሶ መያዝ እንዳለበትና የተያዘውም ታክስ መከፈል እንዳለበት የማረጋገጥ ኃላፊነት ያለበት ማንኛውም የድርጅቱ ሠራተኛ እያንዳንዳቸው ብር 2 ሺ ቅጣት ይከፍላሉ፤
- ከተከፋይ ሒሳብ ላይ ተቀንሶ የሚከፈልን ታክስ ለማስቀረት በማሰብ ከተከፋይ ሒሳብ ላይ ታክስ ቀንሶ የመክፈል ግዴታ ላለበት ሰው (ለሰብሳቢው ሰው) ዕቃዎችን/አገልግሎቶችን ለማቅረብ ፈቃደኛ ያልሆነ ሰው (ሻጭ) ብር 10 ሺ ቅጣት ይከፍላል፤

ምንጭ:- ታክስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር **983/2008** አንቀጽ **106 (1-4)**

### III.1.7. ከተጨማሪ እሴት ታክስ (VAT) ጋር የተያያዙ ቅጣቶች

- ለተጨማሪ እሴት ታክስ መመዝገብ ያለበት ሰው ሳይመዘገብ የቀረ እንደሆነ መመዝገብ ከነበረበት ቀን ጀምሮ እስካመለከተበት ድረስ ላለው ለእያንዳንዱ ጊዜ ብር 2 ሺ ቅጣት ይከፍላል፤
- በቆይታ ጊዜ ከሚጣለው ቅጣት በተጨማሪ መመዝገብ ከነበረበት ቀን ጀምሮ ለመመዝገብ እስካመለከተበት ቀን ወይም በግብር አስገቢው አነሳሽነት እስከተመዘገበበት ቀን ድረስ VAT የሚከፈልበት ግብይት ላይ ሊከፈል ይገባ የነበረውን 15% VAT 100% ቅጣት ይከፍላል፤
- ማንኛውም ሰው ሆን ብሎ በግብይቱ ላይ መከፈል የሚገባውን VAT ለማሳነስ (ተመላሽ የሚደረገውን የታክስ መጠን ለመጨመር) በማሰብ ሀሰተኛ የታክስ ደረሰኝ ከሰጠ ብር 50 ሺ ቅጣት ይከፍላል፤

ምንጭ:- ታክስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር **983/2008** አንቀጽ **107 (1-4)**

### III.1.8. የታክስ ደረሰኝ አለመስጠት

- ደረሰኝ መስጠት ሲገባው ያልሰጠ ማንኛውም ታክስ ከፋይ ለገዥ ባልሰጠው በእያንዳንዱ ደረሰኝ ብር 50 ሺ ቅጣት ይቀጣል።

### III.1.9. ታክስን አሳንሶ ማሳወቅ የሚያስከትለው ቅጣት

- በታክስ ማስታወቂያ የተገለጸው የታክስ መጠን ታክስ ከፋዩ ሊከፍል ከሚገባው ትክክለኛ የታክስ መጠን ያነሰ እንደሆነ የታክስ ጉድለት ልዩነት እና የልዩነቱን መጠን በ 10% ይቀጣል። ይህንኑ ከደጋገመ ልዩነቱ ከ 30-50% ከፍ ይለል፤

ምንጭ:- ታክስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር **983/2008** አንቀጽ **108፣ 109 (1-3)**

### 3.1.10. ታክስን በመሸሸ የሚጣል ቅጣት

- ባለሥልጣኑ የታክስ ከፋይን የታክስ ስሌት ሲሠራ ከታክስ መሸሸን የሚከላከል ድንጋጌ ተፈጻሚ ካደረገ ታክስ ከፋዩ ይህ ድንጋጌ ተፈጻሚ ባይደረግ ኖሮ ከታክስ በመሸሸ ሊያስቀር ይችል የነበረውን የታክስ መጠን እጥፍ ቅጣት ይከፍላል።

3.1.10. ከሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያ ጋር ተያይዞ የሚጣል ቅጣት

- በባለሥልጣኑ ዘንድ ያልተመዘገበ መሣሪያ ወይም የሽያጭ ሶፍትዌር ከተጠቀመበት ለእያንዳንዱ መሣሪያ ብር 50 ሺ ቅጣት ይከፍላል፤
- ሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያ እያለ በሌላ ደረሰኝ ከተጠቀመ 50 ሺ ሲቀጣ ማሽኑ ላይ ጉዳት ሲያደርስ 100 ሺ ይቀጣል።

## 3.2. የታክስ ወንጀሎች

- በታክስ ላይ የሚፈፀሙ ወንጀሎች ክሱ የሚመሰረተው፣ የሚታየውና ይግባኝም የሚቀርበው በኢትዮጵያ የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ሥነ-ሥርዓት መሠረት ይሆናል፤
- ማንኛውም ሰው ከአንድ በላይ የታክስ ከፋይ መለያ ቁጥር ለመውሰድ የሞከረ፣ የታክስ ከፋይ መለያ ቁጥሩን ሌላ ሰው እንዲጠቀምበት የሰጠ ወይም የሌላን ሰው የታክስ ከፋይ መለያ ቁጥር የተጠቀመ እንደሆነ ብር 20 ሺ እና ከ 1 እስከ 3 ዓመት በሚደርስ ቀላል እሥራት ይቀጣል፤
- ማንኛውም ሰው ሆነ ብሎ ወይም በከባድ ቸልተኝነት ለግብር ሰበሳቢው ሀሰተኛ መግለጫ የሰጠ/የተጭበረበሩ ሰነዶችን ያቀረበ እንደሆነ ከብር 50 ሺ እስከ 100 ሺ በሚደርስ ቅጣት እና ከ 3-15 ዓመት በሚደርስ ጽኑ እሥራት ይቀጣል፤
- ሀሰተኛ ደረሰኞችን ለመሥራት/ለማተም የሚያገለግል ማሽን የያዘ፣ የሸጠ፣ ያከራየ ወይም በሌላ መንገድ ያቀረበ ማንኛውም ሰው ብር 200 ሺ እና ከ 10-15 ዓመት በሚደርስ ጽኑ እሥራት ይቀጣል፤
- ሀሰተኛ ደረሰኞችን የያዘ፣ ያስቀመጠ፣ ለሽያጭ ያመቻቸ ሰው ከ 3-5 ዓመት በሚደረስ ጽኑ እሥራት ይቀጣል፤

ምንጭ:- ታክስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር **983/2008** አንቀጽ **116-119.**

### 3.2.1. የተጭበረበሩ (ሕገ-ወጥ የሆኑ) ደረሰኞች

- ማንኛውም ሰው የተጭበረበሩ ደረሰኞችን ያዘጋጀ፣ ያተመ፣ የሸጠ ወይም ያሰራጨ ወይም የታክስ ዕዳውን ለመቀነስ ወይም ተመላሽ ለመጠየቅ የተጭበረበሩ ደረሰኞችን የተጠቀመ እንደሆነ ብር 100 ሺ እና ከ 7-10 ዓመት በሚደርስ ጽኑ እሥራት ይቀጣል፤
- ሀሰተኛ ደረሰኞችን፣ ለማዘጋጀት/ለማተም የሚያገለግል ማሽን፣ መሳሪያ፣ ወይም ሶፍትዌር የያዘ፣ የሸጠ፣ ያከራየ ወይም በሌላ መንገድ ያቀረበ ማንኛውም ሰው ብር 200 ሺ የገንዘብ ቅጣት እና ከ 10-15 ዓመት ጽኑ እሥራት ይቀጣል፤
- ሀሰተኛ ደረሰኞችን የያዘ፣ ያስቀመጠ፣ ለሽያጭ ያመቻቸ ወይም ሀሰተኛ ደረሰኞች ጥቅም ላይ እንዲውሉ ያደረገ ሰው ከ 3-5 ዓመት በሚደረስ ጽኑ እሥራት ይቀጣል፤
- ግብይት ሳይፈጸም ደረሰኝ የሰጠ ወይም የተቀበለ ሰው ከብር 100 ሺ እስከ ብር 200 ሺ ቅጣት እና ከ 7-10 ዓመት በሚደርስ ጽኑ እሥራት ይቀጣል፤

### 3.2.2. አግባብ ያልሆነ ተመላሽን መጠየቅ

- ባለሥልጣኑን ለማጭበርበር በማሰብ ተመላሽ ወይም ማካካሻ የጠየቀ ሰው ብር 50 ሺ እና ከ 5-7 ዓመት በሚደርስ ጽኑ እሥራት ይቀጣል።

### 3.2.3. የተጨማሪ እሴት ታክስ ወንጀሎች

- ለተጨማሪ እሴት ታክስ ሳይመዘገብ የታክስ ደረሰኝ የሰጠ ሰው ብር 200 ሺ የገንዘብ ቅጣት እና ከ 7-10 ዓመት በሚደርስ ጽኑ እሥራት ይቀጣል፤

- ለተጨማሪ እሴት ታክስ የተመዘገበ ማንኛውም ሰው VAT አዋጅ መሠረት የታክስ ዴቢት/ክሬዲት ማስታወሻ ለመስጠት ፈቃደኛ ካልሆነ ወይም VAT አዋጅ ከተፈቀደው ውጪ የታክስ ዴቢት ወይም ክሬዲት ማስታወሻ የሰጠ እንደሆነ ብር 10 ሺ የገንዘብ ቅጣት እና በአንድ ዓመት ቀላል እሥራት ይቀጣል፡፡

### 3.2.4. ታክስን ለማስከፈል ከሚወሰድ እርምጃ ጋር የተያያዙ ወንጀሎች

- ማንኛውም የታክስ ከፋይ ንብረት ተረካቢ በታክስ ሕጎች በተደነገገው መሠረት የተጣለበትን ግዴታ ሳይፈፅም የቀረ እንደሆነ በብር 5 ሺ የገንዘብ ቅጣት እና በአንድ ዓመት ቀላል እሥራት ይቀጣል፤
- የንብረት መያዝ ትዕዛዝ የደረሰው ሰው ትዕዛዙ የተላለፈበትን ንብረት የሸጠ፣ የለወጠ ወይም ትዕዛዙ የተላለፈበትን ንብረት የደበቀ፣ የሰበረ፣ ያበላሸ እንደሆነ ወይም ትዕዛዙ የተላለፈበትን ንብረት የሚመለከት ማናቸውንም ሰነድ ያወደመ፣ የደበቀ፣ ያስወገደ፣ የጎዳ፣ የለወጠ፣ የሰረዘ፣ የደለዘ ወይም ያጠፋ እንደሆነ ከ 2-3 ዓመት በሚደርስ ቀላል እሥራት ይቀጣል፡፡

### 3.2.5. ታክስን መሰወር

- ማንኛውም ሰው ታክስን ለመሰወር በማሰብ ገቢውን የደበቀ፣ የታክስ ማስታወቂያውን ያላቀረበ ወይም ታክሱን ያልከፈለ እንደሆነ ከብር 100 ሺ-200 ሺ ቅጣት እና ከ 3-5 ዓመት ጽኑ እሥራት ይቀጣል፤
- ከተከፋይ ሒሣብ ላይ ታክስን ቀንሶ ገቢ የማድረግ ኃላፊነት የተጣለበት ሰው ታክስን ለመሰወር በማሰብ ቀንሶ የያዘውን ታክስ ለመንግሥት ያላስተላለፈ ከሆነ ከ 3-5 ዓመት በሚደርስ ጽኑ እሥራት ይቀጣል፡፡

### 3.2.6. ሥልጣን ሳይኖር ታክስ መሰብሰብ

- ታክስ እንዲሰበስብ ሥልጣን ያልተሰጠው ማንኛውም ሰው ማንኛውንም ታክስ የሰበሰበ እንደሆነ ከብር 50-75 ሺ በሚደርስ ቅጣት እና ከ 5-7 ዓመት በሚደርስ ጽኑ እሥራት ይቀጣል፡፡

### 3.2.7. ከ CR ጋር በተገናኘ ወንጀሎች

- በባለሥልጣኑ ያልተመዘገ CR የተጠቀመ ሰው ከ 3-7 ዓመት ጽኑ እሥራት ይቀጣል፤
- መሣሪያው በጥገና ላይ ባለበት ጊዜ (በሌላ በቂ ምክንያት) ካልሆነ በስተቀር በ CR ከታተመ ደረሰኝ ውጪ ወይም ያለደረሰኝ ግብይት ካከናወነ ከ 2-5 ዓመት ጽኑ እሥራት ይቀጣል፤
- በ CR የፊስካል ማስታወሻ ላይ ጉዳት ያደረሰ/እንዲቀየር ያደረገ 3-5 ከዓመት በማይበልጥ ጽኑ እሥራት ይቀጣል፤

- ማንኛውም ሰው CR ወይም ሶፍትዌር አቅራቢነት ፈቃድ ሳይኖረው ማንኛውንም የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያ ወይም ሶፍትዌር ለገበያ ያዋለ እንደሆነ ከ 5-7 ዓመት ጽኑ እሥራት ይቀጣል፤

### 3.2.8. በድርጅቶች የሚፈፀሙ የታክስ ወንጀሎች

- **የታክስ ሕግን በመተላለፍ ወንጀል የፈፀመው ድርጅት በሚሆንበት ጊዜ ወንጀሉ በተፈፀመበት ወቅት ሥራ አስኪያጅ የሆነ ማንኛውም ሰው ወንጀሉን እንደፈፀመ ይቆጠራል (ጥፋትን ለመከላከል ብሎ ወንጀሉን የፈፀመ ከሆነ ሊታይለት ይችላል)።**

**ምንጭ:-ታክስ አስተዳር አዋጅ ቁጥር 983/2008 አንቀጽ 116-132**

**3.3.** ሽልማቶች

**3.3.1.** የታክስ ስወራን በሚመለከት ለተሰጠ ተጨባጭ መረጃ የሚሰጥ ሽልማት **(983/2008 አ 134)**

i. ማንኛውም ሰው በመደበቅ፣ አሳንሶ በማሳወቅ፣ በማጭበርበር ወይም በሌላ ተገቢ ባልሆነ መንገድ የሚፈፀምን የታክስ ስወራ አስመልክቶ ሊረጋገጥ የሚችል ተጨባጭና የማያሻማ መረጃ ለባለሥልጣኑ የሰጠ እንደሆነ ባለሥልጣኑ በሚያወጣው መመሪያ መሠረት የተሰወረውን ታክስ መጠን እስከ 2 0% /ሃያ በመቶ/ በሽልማት መልክ ታክሱ በሚሰበሰብበት ጊዜ ለዚህ ሰው ይሰጣል።

ii. በተራ ቁጥር i

ሀ. በታክስ ስወራው ተግባር ላይ ለተሳተፈ፣ ወይም

ለ. የታክስ ስወራውን ማሳወቅ የመደበኛ ሥራው አካል ለሆነ ሰው ተፈፃሚ አይሆንም።

**ሙከራ ሶስት**

1. በታክስ የሚፈጸሙ የአስተዳደራዊ እና የወንጀል ቅጣቶች እንዲሁም ሽልማቶች አብራሩ?

## ክፍል አራት
## አስተዳደራዊ ቅጣት አነሳስ

አስተዳደራዊ ቅጣት በከፊል ወይም ሙሉ በሙሉ ሊነሳ ይችላል። ይሄም ታክስ ከፋዮች፤ ታክስ ከፋይ ሆነው እንዲቀጥሉና ውዝፍ ፍሬ ታክሱን እንዲከፍሉ ታሳቢ በማድረግ ነው። አስተዳደራዊ ቅጣት ማንሳት የወጪ መጋራትን እና የጡረታ መዋጮን አይጨምርም። አስተዳደራዊ ቅጣት ተመርምሮ የሚነሳ ከሆነ የሚያነሳው የአወሳሰንና አሰባሰብ የሥራ ሂደት ነው።

በውሳኔው ቅር የተሰኘ አካል በቅርንጫፉ ውስጥ ባለው ታክስ ቅሬታ አጣሪ የሥራ ክፍል ማቅረብ እንደሚችል መመሪያው በቁጥር 2(2) ደንግጓል። በዚህ ቅጣት አነሳስ ውስጥ ታክስ ከፋዩ ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት ሊያስወግደው ካልቻለ፡-

- ከሰው ሰራሽ አደጋ፤
- ከፍተኛ የተፈጥሮ አደጋ፤
- ፅኑ ህመም፤
- ታክስ መክፈል የማይችል መሆኑን ማስረጃ ሲኖር...

### IV.1. አስተዳደራዊ ቅጣት በከፊል የሚነሳበት ምክንያት

- በተደነገጉት የቅጣት ደረጃዎችና
- የታክስ ዕዳው የተከፈለበትን ጊዜ መሰረት በማድረግ።

#### IV.1.1. ዝቅተኛ የቅጣት ደረጃ (ከ 30-90%) ይነሳል

- ከምዝገባ እና ስረዛ ጋር የተያያዙ ቅጣቶች፤
- ከታክስ ከፋይ መለያ ቁጥር /TIN/ ጋር የተገናኘ ቅጣት በአግባቡ ያለመጠቀም፤
- ታክስን ዘግይቶ ማሳወቅ እና ዘግይቶ መክፈል፤

ምንጭ:- ታክስ አስተዳር አዋጅ ቁጥር **983/2008** አንቀጽ **101-113**

#### IV.1.2. መካከለኛ የቅጣት ደረጃ (ከ 20-80%) ይነሳል

- ከተከፋይ ሒሣብ ላይ ተቀንሶ ከሚከፈል ታክስ ጋር በተገናኘ የሚጣል ቅጣት፤

- ከሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያ ጋር ተያይዞ የሚጣል ቅጣት፤
- ማንኛውንም የባንክና የማሽን አድራሻ ለውጥ ያላሳወቀ ታክስ ከፋይ ብር 20 ሺ እና
- ግንኙነት ካለው ሰዎች ጋር የሚያደርጋቸውን ግብይቶች ዝርዝር ጉዳይ ለባለሥልጣኑ ያልገለጸ ሰው ብር 10 ሺ ሲቀጣ

ምንጭ:- ታክስ አስተዳር አዋጅ ቁጥር **983/2008** አንቀጽ **106፣ 113 (1፣2)፣ 114(1፣6)**

**4.2.3.**ከፍተኛ የቅጣት ደረጃ **(**ከ **10-70%)** ይነሳል

- ሰነዶችን ባለመያዝ የሚጣል ቅጣት እና
- ማንኛውም ሰው ሆን ብሎ በግብይቱ ላይ መከፈል የሚገባውን VAT ለማሳነስ ወይም በግብይቱ ላይ ተመላሽ የሚደረገውን የታክስ መጠን ለመጨመር በማሰብ ትክክለኛ ያልሆነ የታክስ ደረሰኝ የሰጠ እንደሆነ ብር 50 ሺ ሲቀጣ፤
- የታክስ ደረሰኝ ባለመስጠት ብር 50 ሺ ሲቀጣ እና ታክስን በመሸሸ ሲቀጣ፤
- ለታክስ ሰብሳቢው የተጠየቀ መረጃ ባለመስጠት 5 ሺ ሲቀጣ

ምንጭ:- ታክስ አስተዳር አዋጅ ቁ**. 983/2008** አንቀጽ **102፣ 107(4)፣ 108፣ 110፣ 114(7)**

**IV.2.** የቅጣት አነሳስ ምጣኔ በደረጃ መሠረት

| ተ.ቁ | ፍሬ፣ወለድና መቀጮ የተከፈለበት ግዜ | የቅጣት አነሳስ ምጣኔ በደረጃ መሰረት | | |
|---|---|---|---|---|
| | | ዝቅተኛ | መካከለኛ | ከፍተኛ |
| 1 | ታክስ ከፋዩ፤ ማስታወቂያ፣ የቅሬታ፣ የፍ/ቤት ውሳኔ ደርሶት | | | |
| | በ 30 ቀናት ውስጥ ቀርቦ ከከፈለ | 90 | 80 | 70 |
| | ውል ገብቶ በ 6 ወራት ውስጥ ከፍሎ ካጠናቀቀ | 80 | 70 | 60 |
| | ውል ገብቶ ከ 6 ወራት በላይ ከፈጀበት | 70 | 60 | 50 |
| 2 | ባለመክፈሉ ማስጠንቀቂያ ሳይደርሰው ንብረቱ ከተያዘ በኋላ | | | |
| | በአንድ ጊዜ አጠቃሎ ከከፋለ | 80 | 70 | 60 |
| | ውል ገብቶ በ 6 ወራት ውስጥ ከከፈለ | 70 | 60 | 50 |
| | ውል ገብቶ ከ 6 ወራት በላይ ከፈጀበት | 60 | 50 | 40 |
| 3 | ባለመክፈሉ ሃብቱ ተይዞ የመያዣ ማስጠንቀቂያ ከተሰጠ በኋላ | | | |
| | በአንድ ወር ውስጥ አጠቃሎ ከከፈለ | 70 | 60 | 50 |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| | ውል ገብቶ በ 6 ወራት ውስጥ ከከፈለ | 60 | 50 | 40 |
| | ውል ገብቶ ከ 6 ወራት በላይ ከፈጀበት | 50 | 40 | 30 |
| | | | | |

| ተ.ቁ | ፍሬ፣ወለድና መቀጮ የተከፈለበት ግዜ | የቅጣት አነሳስ ምጣኔ በደረጃ መሰረት | | |
|---|---|---|---|---|
| | | ዝቅተኛ | መካከለኛ | ከፍተኛ |
| 4 | ባለ መክፈሉ ሃብቱ ከተያዘ በኋላ ጫረታ ሳይወጣበት | | | |
| | በ አንድ ጊዜ ቀርቦ ከከፈለ | **60** | **50** | **40** |
| | ውል ገብቶ በ **6** ወራት ውስጥ ከፍሎ ካጠናቀቀ | **50** | **40** | **30** |
| | ውል ገብቶ ከ **6** ወራት በላይ ከፈጀበት | **40** | **30** | **20** |
| **5** | ታክስ ከፋዩ የሚፈለግበትን ታክስ ጫረታ ከወጣበት በኋላ | | | |
| | በ **10** ቀናት ውስጥ አጠናቆ ከከፈለ | **50** | **40** | **30** |
| | ውል ገብቶ በ **6** ወራት ውስጥ ከከፈለ | **40** | **30** | **20** |
| | ውል ገብቶ ከ **6** ወራት በላይ ከፈጀበት | **30** | **20** | **10** |

### IV.3. አስተዳደራዊ ቅጣትን ሙሉ በሙሉ ማንሳት

አስተዳደራዊ ቅጣትሙሉ በሙሉ የሚነሳበት አግባብ

- ታክስ ከፋዩ ግዴታውን ለመወጣት ከአቅም በላይ ምክንያት ሲያጋጥመው፤
- ድርጅቱ ንግድ ሥራውን የማይቀጥልና የከሰረ መሆኑን ፍ/ቤት ሲያረጋግጥ፤
- ታክስ ሰብሳቢው የነጋዴውን ሒሳብ ከመመርመሩ በፊት ታክስ ከፋዩ አስተካክሎ ፍሬ፣ ወለድ፣ ቅጣቱን አምኖ በራሱ ከከፈለ፤
- ከንብረቱ 20% በአደጋ መውደሙን የመንግሥት አካል ካረጋገጠለት፤
- የታክስ ውሳኔ በደረሰው በ 30 ቀናት ውስጥ ፍሬ ታክሱን ወለድ እና ጥቃቅን ቅጣቶች ሙሉ በሙሉ ከፍሎ ከጨረሰ፤
- ለቅጣቱ ምክንያት የሆነው ታክስ ሰብሳቢ.ው መ/ቤት የፈጠረው ስህተት ከሆነ።

### IV.4. አስተዳደራዊ ቅጣትን በልዩ ሁኔታ ማንሳት

በመመሪያ ቁጥር 137/2010 ቁጥር 5፣ 6 እና 7 አገባብ ቢኖርም በኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊ እና አስተዳደራዊ ምክንያት ዝርዝር የውሳኔ ሃሳብ የቀረበለትን መርምሮ የገቢ ሰብሳቢ ዋና ዳይሬክተር/የተወከለው ሰው ቅጣቱን ሙሉ ለሙሉ/በከፊል ሊያነሳ ይችላል፤ ውሳኔውም በዚህ መመሪያ ቁጥር 9(2) ይፈፀማል፡፡

**IV.5.** በክፍያ ስምምነት ጊዜ የቅጣት አነሳስ

በክፍያ ስምምነት ጊዜ ቅጣት የሚነሳው በውሉ ውስጥ ሆኖ ፍሬ ታክሱን እና ወለዱን ከፍሎ ማጠናቀቁ ሲረጋገጥ መቀጫው እንደ አግባብነቱ ይነሳል፡፡

**IV.6.** የማይነሳ አስተዳደራዊ ቅጣት

የጡረታ መዋጮ እና የከፍተኛ ትምህርት ወጪ መጋራት በወቅቱ ባለመክፈል የተጣለ ቅጣት አይነሳም፡፡

ሙከራ አራት

1. አስተዳደራዊ ቅጣት በከፊል ወይም ሙሉ በሙሉ የሚነሳባቸውን እና የማይነሳባቸውን ምክንያቶች ዘርዝሩ?

## ማጠቃለያ

ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ የታክስ ገቢ ሰብሳቢ እንደመሆኑ የታክስ ሕግ ተገዥነትን የማሳደግ ዓላማውን ለማሳካት ከሚጠቀምባቸው ስትራቴጂዎች አንዱ የታክስ ትምህርት ነው፡፡ የታክስ ትምህርት አጠቃላይ ዓላማ በፈቃደኝነት ታክስ የመክፍል ባህልን በሕብረተሰቡ ውስጥ ማስረጽ በመሆኑ የታክስ ጉዳዮች ትምህርት ዳይሬክቶሬት ከቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤቶች የታክስ ትምህርት እና መረጃ አቅርቦት የሥራ ሂደት/ቡድን ጋር በመቀናጀት የታክስ ትምህርትን እያስተማሩ ይገኛሉ፡፡ እያስተማሩ ከሚገኙት የታክስ ትምህርት ውስጥ ከታክስ ጋር በተገናኘ የሚፈጠር አለመግባባት፣ የታክስ አስተዳደር እና የወንጀል ቅጣቶች እንዲሁም **አስተዳደራዊ ቅጣት አነሳስ በዚህ ሞጁል የተዳሰሱት ናቸው፡፡ እነዚህን ርዕሰ ጉዳዮች ወደ ተግባር መቀየር የገቢዎች ሚኒስቴርን እና የግብር ከፋዩን ግንኙነት ሰላማዊ ያደርገዋል፡፡**

## ማጣቀሻ

- *በፌደራል የታክስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር* 983/2008
- *ታክስ አስተዳደር ቅጣት አነሳስ መመሪያ ቁጥር* 137/2010 የተሰጠ ትርጉም *ይይዛሉ።*
- *በግብር/ታክስ በሚፈጸሙ አስተዳደራዊ እና የወንጀል ቅጣቶች ዙሪያ በገቢዎች ሚኒስቴር ባህር ዳር ቅርንጫፍ ጽ/ቤት በታክስ ሕግ ተገዢነት ዘርፍ  የታክስ ከፋዮች ትምህርትና መረጃ አቅርቦት ቡድን የካቲት/*2013 *ዓ.ም. የተዘጋጀ የስልጠና ሞጅል*
- በግብር/ታክስ ለሚፈጸሙ ወንጀሎች አስተዳደራዊ ቅጣቶች  ላይ በአቶ አዲሱ ይርጋ ሺበሺ፣ አቶ እንዳለ ነጋሽ አጥላባቸው፣አቶ ጌታቸው ሽፈራው መሸሻ፣ አቶ አዱኛ ደበሳ አምበሊ፣ አቶ ጠንክር ምኑታ አንቅነዳ፣ አቶ በዕውቀቱ ዳኛቸው አረጋ፣ አቶ አብረሐም ለታ ገደፋ፣ አቶ አሸናፊ ባይሳ እሬንሶ ነሐሴ 2011 ዓ.ም የተዘጋጀ የሥልጠና ሰነድ።